ቁጥር-OFAGF-03-5/1/128
ቀን 29/4/2012

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለተከበሩ አቶ ፍቃዱ ተሰማ

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

የስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 8 ገጽ የኦዲት ሪፖርት ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሠላምታ ጋር

በየነ ኮሬ

ፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክተር
Finance & Communication Organization
Audit Director

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
  (ከ8 ገጽ የኦዲት ሪፖርት ፣
  44 ገጽ የስራ አመራር ሪፖርት እና
  21 ገጽ የሂሳብ መግለጫዎች)
  <u>አዲስ አበባ</u>

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ /2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን
የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የተመደበለትን የመደበኛና ካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን የዓለም አቀፍ የዋና ኦዲተሮች የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኮርፖሬሽኑ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች

የኮርፖሬሽኑ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1.ውዝፍ የዱቤ ተሰብሳቢ ሂሳብ

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 858/2007 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ላይ በተገለጸውና በ2011 በጀት ዓመት በጸደቀው የገቢ እቅድ መሰረት ገቢውን በሚገባ እየሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የኢትዮጵያ ብሮድካስትንግ ኮርፖሬሽን ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ በገቡት ውል መሰረት የሚያስከፍለው ክፍያ የድርጅቱ ዋንኛው የገቢ ምንጭ በመሆኑ ከ2002-2011 ዓ/ም በዱቤ የተሰጠ የማስታወቂያ አገልግሎት በድምር ብር 59,349,255.46 ያልተሰበሰበ ውዝፍ የዱቤ ሂሳብ ያለ ሲሆን ከ2002 - 2010 ያለውን በ2010 በጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እስካሁን ያልተሰበሰበ መሆኑ፤

2 ዓመታዊ ውል ከተያዘላቸው ማስታወቂያዎች አገልግሎት መሰብሰብ ከነበረበት ገቢ በማነስ የተሰበሰበ፤

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ በተገባው ውል የሚያስከፍለው ክፍያ የድርጅቱ ዋንኛው የገቢ ምንጭ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ ምርትና አገልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ በተገባው ውል መሰረት ገቢውን እየሰበሰበ መሆኑ ለማረጋገጥ ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ:-

ከካክተስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት የአገልግሎት ዋጋ መጠየቂያ ደረሰኝ ወይም ኢንቮይስ ላይ ያለው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ብር 5,710,955.55 ቢሆንም በእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኙ ላይ ገቢ የሆነው የክፍያ መጠን ብር 4,377,741.48 በመሆኑ ፤የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ላይ ገቢ የሆነው የገንዘብ መጠን በብር 1,333,214.07 በማነስ የሚያሳይ በመሆኑ ገቢው በአግባቡ ያለተሰበሰበ መሆኑ፤

3. <u>የክፍያ ተመን የሌለው የቀን ሠራተኛ ክፍያ</u>

የፌደራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4፣7 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢውን የሰነድ ማስረጃ መቅረቡን፣ወጪ ከመደረጉ በፊት ሰለወጪው የተሟላ ማስረጃ ማቅረብና ሥልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት የሚገልፅ ቢሆንም ኮርፖሬሽኑ በተለያዩ የስራ ዘርፍ ለተሰማሩ የቀን ሰራተኞቹ ስራውን ከሚያሰራው ክፍል እንዲሰራለት የሰው ሃብት አስተዳደርን የጠየቀበት ማስረጃ፣ ስራው እንዲስራ ከሚመለከተው አካል የተፈቀደበት እና ለቀን ሰራተኞች ክፍያ ወቅታዊ የገበያ ጥናት ተደርጎ በሚመለከተው አካል የተሰወነ የክፍያ ተመን ማስረጃ ሳይኖር ብር 229,665.10 የተከፈለ መሆኑ፣

4 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪዉ ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪዉን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩንና ወጪዉ በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ወስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈፀም በኮርፖሬሽኑ የሚፈፀሙ ክፍያዎች መመሪያውን የተከተሉ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

- ☞ በኮርፖሬሽኑ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ ለተገዙ ግዥዎችና የአገልግሎት ክፍያዎች በ2011 በጀት ዓመት ከመደበኛ/ከውስጥ ገቢ/ በጀት ብር 264,975.97 እና ከካፒታል በጀት ደግሞ ብር 23,555,278.00 በድምር ብር 23,820,253.97 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
- ☞ የ2010 ዓ.ም. የብሮድካስት አገልግሎት ዓመታዊ ክፍያ ብር 5,240,294.1165 በወቅቱ ባለመከፈሉ ምክንያት ብር 275,804.95 አላግባብ ለቅጣት የተከፈለ መሆኑ፣
- ☞ የኤሌክትሪክ ክፍያ ከ2008 ሰኔ ወር ጀምሮ እስከ ጥቅምት 2011 ዓ.ም በጥቅል ብር 12,115,628.00 ክፍያው የተፈጸመ በመሆኑ ከሀምሌ 2010 እስከ ጥቅምት 2011 ዓ.ም ክፍያ ቀንሶ ለማስቀመጥ መረጃ ባለመቅረቡ ምን ያህል እንደሆነ ለመለየት ያልተቻለ መሆኑ፣

5 **<u>ያለውድድር የተፈጸመ ግዥ</u>**

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚ አዋጅ ቁጥር 858/2007 መመሪያ ቁጥር 010/2008 ክፍል 5 ተራ ቁጥር 68/ ፊደል መ መሰረት ኮርፖሬሽኑ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ የግዥን በግልጽ ጨረታ የግዢ ዘዴ መፈፀም እንደለበት የሚደነግግ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የእቃዎችና የአገልግሎት ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለመስተንግዶ አገልግሎት ብር 1,246,882.71
- ለሥልጠና አገልግሎት ብር 220,910.40
- ለአዳራሽ ኪራይ ብር 150,747.51

በድምር ብር 1,618,540.62 ያለውድድር በቀጥታ ግዥ በማከናወን ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፤

6. **<u>በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ተስብሳቢ ሂሳብ</u>**

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ፣ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተሰብሳቢ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 4 ከፊደል ሀ-ሰ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት በወቅቱ እየተሰበሰበ መመሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ከመደበኛ/የውስጥ ገቢ/ ሂሳብ ከመደበኛ ሂሳብ ብር 37,691,384.82 እና ከካፒታል ሂሳብ ብር 1,890,479.72 በድምር 39,581,864.54 በወቅቱ ያልተወራረደ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 677,658.89 ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ዕድሜ ያለው፤ ብር 59,725.23 ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት የቆየ ብር 18,341.25 ተሰብሳቢ ሂሳቡ ከማን እንደሚፈለግ እና ምን ያህል ጊዜ ሳይወራረድ እንደቆየ የማይታወቅ፤ ቀሪው ብር 37,098,922.30 ተሰብሳቢ ሂሳብ በኢትየጵያ ንግድ ባንክ ስም የሚታይ ቢሆንም ለምን በተሰብሳቢ እንደተያዘና ምን ያህል ጊዜ ሳይወራረድ እንደቆየ የማይታወቅ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መገኘቱ፤

7. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

በፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ፣ በፌዴራል መንግሰት ሚቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 የተከፋይ ሂሳብ በአንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከፊደል ሀ-ሠ በዝርዝር በተቀመጠው መሰረት ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እየተከፈሉና እየተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

ከመደበኛ/ከውስጥ ገቢ/ ብር 23,624,771.47 እና ከካፒታል በጀት ሂሳብ ብር 2,465,818.20 በድምር ብር 26,090,589.67 በወቅቱ እንዳልተወራረደ ከሚታየው ሂሳብ ውስጥ ብር 1,619,436.20 ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የቆየ ሲሆን በድምር ብር 5,570,541.59 ተከፋይ ሂሳቡ ደግሞ የተከሰተበት ጊዜ፣ የባለጥቅሙ ስም፣ አድራሻ እና የክፍያው ዓይነት የማይታወቅ ሂሳብ መሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ መ/ቤቱ ባቀረበው የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ ሙከራ (tiral Balance) ላይ በ4104 (ሌተር ኦፍ ክሬዲት የተገደበ ሂሳብ) እና በሂሳብ አርእስት 5516 (ሌሎች ተከፋይ) በሚል ብር 886,224.80 የሚታይ ሲሆን በተከፋይ የሂሳብ ሪፖርቱ ላይ ያልተካተተና የማይታይ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 በዝርዝር በተገለጹት ምክንያቶች በእኛ አስተያየት የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡ ፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች</u>

1. <u>የገቢ ዕቅድ አፈፃፀም</u>

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 858/2007 ክፍል ሁለት አንቀጽ 14 ላይ በተገለጸውና በ2011 በጀት ዓመት በጸደቀው የገቢ እቅድ መሰረት ገቢውን እየሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

- በ2011 በጀት ዓመት ብር 500,000,000.0 (አምስት መቶ ሚሊዮን) ለመሰብሰብ የታቀደ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ተሰብስቦ ሪፖርት የተደረገው የገንዘብ መጠን ብር 264,268,140.49 ብቻ በመሆኑ እቅዱ ከአፈጻጸሙ/ ክንውኑ/ ጋር ሲነጻጸር በብር 235,731,859.51 ወይም (47%) በመቶ በማነስ የሚያሳይ መሆኑ፤

* ኮርፖሬሽኑ በበጀት ዓመቱ በእቅዱ መሰረት ገቢውን ሊሰበስብ ባለመቻሉ በበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት በድምር ብር 275,790,742.91 የሚያሳይ ሲሆን የተሰበሰበው የገቢ ሂሳብ ሪፖርት በድምር ብር 264,268,140.49 በመሆኑ ብር 11,522,602.42 የመደበኛ/የውስጥ ገቢ/ በጀት ዓመታዊ የወጪ ሂሳብ ከገቢው በመብለጥ በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የሚታይ መሆኑ፤

2. ስራ ላይ ያልዋለ በጀት

የፌዴራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ መ/ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ በፕሮግራም ከተደለደለው መደበኛ በጀት ከ10% በመቶ በላይ የሆነውን ንጽጽር በማድረግ ሲታይ ፡-

1. ከመደበኛ በጀት

• ፕሮግራም 4290101	ብር	59,718,837.24
• ፕሮግራም 4290202	ብር	4,127,067.19
• ፕሮግራም 4290303	ብር	10,382,465.57
• ፕሮግራም 4290404	ብር	9,878,723.20
• ፕሮግራም 4290505	ብር	14,027,962.65
• ፕሮግራም 4290606	ብር	5,032,828.86
• ፕሮግራም 4290707	ብር	1,559,661.48
ድምር		104,727,546.19

በድምር ብር 104,727,546.17 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑ በኦዲት ታውቋል፡፡

ሌሎች ጉዳዮች

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

<u>የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ድክመቶች</u>

- በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ከአንቀፅ 65-68 እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት ኮርፖሬሽኑ ለንብረቶቹ ተገቢው ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-
  - በዋናው መ/ቤትም ሆነ በቅርንጫፍ መ/ቤቶች የቋሚና የአላቂ የንብረት ቆጠራ የተጀመረ ቢሆንም ቆጠራው ባለመጠናቀቁ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፣ የተሽከርካሪ ስፔር ፓርቶች ተመላሽ በሚደረግበት ወቅት በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ የማይደረግ መሆኑ፣
- የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4 መሰረት በየወሩ የደመወዝ ዝግጅት ከመደረጉ በፊት ሰራተኞቹ ስራ ላይ ስለመገኘታቸው የሚቆጣጠሩበት የሰዓት ፊርማ (attendance) የሌላቸው እና ወሩ በገባ በ20ኛው ቀን ሠራተኞች በሥራ ላይ ለመሆናቸው የሥራ ክፍሎቹ ለፋይናንስ ክፍል ማሳወቅ እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ ኮርፖሬሽኑ በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-የኮርፖሬሽኑ የስራ ክፍሎች ሰራተኞች በስራ ላይ መገኘታቸውን የሚቆጣጠርበት የሰዓት ፊርማ የሌላቸው እና በወሩ በሥራ ላይ ለመሆናቸው ለፋይናንስ ክፍል ሳያሳውቅ የደመወዝ ክፍያ የሚፈጸም መሆኑ ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት